መልእክት ስድስት

**በኤርሚያስ መጽሐፍ እንደ ተገለጠው ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የመሆን መርህ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 2፡8-9፣ 16-17፤ ኤር. 2፡13፤ 15፡16፣ 19፤ 23፡5-6፤ 31፡31-34፤ 40፡5-6፣ 13-14

1. **እግዚአብሔር ከሰው ጋር አንድ ለመሆን እና ሰውም ከእርሱ ጋር አንድ እንዲሆን ያለው መሻት እግዚአብሔር እና ሰው በመልኮቻቸው እና በምሳሌዎቻቸው ባላቸው መመሳሰል ሊታይ ይችላል፦**
   - ሀ. በእግዚአብሔር በመፍጠር ሂደት የተፈጠረ "የሰው ወገን" አልነበረም፤ ይልቁንም፣ እግዚአብሔር የፈጠረው እንደ የገዛ ወገኑ፣ ይኸውም፣ እንደ የእግዚአብሔር-ወገን ነበር፤ እግዚአብሔር ሰው እርሱን እንዲገናኝ እና እርሱን እንዲቀበለው መንፈስ እንዲኖረው በሕይወት እስትንፋስ ፈጠረው—ዘፍ. 1፡24-26፤ 2፡7።
   - ለ. በዘፍጥረት 18፡2-13 ሦስት ሰዎች ለአብርሃም ተገለጡለት፤ ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ክርስቶስ—ያሕዌ—ነበር እንዲሁም ሌሎቹ ሁለቱ መላእክት ነበሩ (19፡1)፤ ይህ ማለት ሥጋ ከመልበሱ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ወዳጁን አብርሃምን ሲጎበኝ እንደ ሰው ተገልጧል—2 ዜና. 20፡7፤ ኢሳ. 41፡8፤ ያዕ. 2፡23።
   - ሐ. የእግዚአብሔር መልአክ (እግዚአብሔር፣ ያሕዌ፣ የእግዚአብሔር ሰው—ክርስቶስ) ከክርስቶስ ተሠግዎ በፊት ለማኑሄ እና ለሚስቱ ተገለጠላቸው—መሣ. 13፡3-6፣ 22-23።
   - መ. ዳንኤል ከክርስቶስ ተሠግዎ በፊት የሰው ልጅ የሆነውን የክርስቶስን ራእይ አየ፤ በዳንኤል 7፡13-14 መሠረት፣ ዳንኤል የሰው ልጅ ከሰማይ ደመናት ጋር ሲመጣ አየ፣ እንደውም በዘመናት ወደ ሸመገለው—ወደ የዘላለም አምላክ—መጣ ወደ ፊቱም አቀረቡት፤ ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጥቶት ነበር፤ ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፣ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው።
   - ሠ. አዳም የክርስቶስ ምሳሌ፣ ቅድመ ማሳያ ነው—ሮሜ 5፡14።
   - ረ. ክርስቶስ የማይታየው አምላክ ምሳሌ ነው—ቆላ. 1፡15።
   - ሰ. ቃል (እግዚአብሔር) የሥጋ ኃጢአት ሳይኖረው (2 ቆሮ. 5፡21፤ ዕብ. 4፡15) በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በመምጣት (ሮሜ 8፡3) ሥጋ ሆነ (ዮሐ. 1፡14)።
   - ሸ. በእግዚአብሔር መልክ የሚኖረው ክርስቶስ በሰዎች ምሳሌ በመሆን እና በመልኩም እንደ ሰው በመገኘት በተሠግዎው የባሪያን መልክ ያዘ—ፊልጵ. 2፡6-8።
   - ቀ. እስጢፋኖስ ሰማያት ተከፍተው የሰውን ልጅ—ክርስቶስን—በእግዚአብሔር ቀኝ አየው (ሐዋ. 7፡56)፤ ይህ የሚያመለክተው ክርስቶስ ወደ ሰማያት ከዐረገ በኋላ አሁንም የሰው ልጅ እንደ ሆነ ነው (ከእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ፣ #132'ን ይመልከቱ)።
   - በ. በማቴዎስ 26፡64 ጌታ ኢየሱስ፣ "ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በኃይል [በእግዚአብሔር] ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ" አለ፤ ይህ የሚያሳየው ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣም የሰው ልጅ እንደሆነ ነው።
   - ተ. ጳውሎስ በሮሜ 8፡29 እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን (እኛ አማኞችን)፣ የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ እንደ ወሰናቸው፣ ይኸውም እርሱ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ እንደ ሆነ ይነግረናል፤ ብዙ ወንድሞቹ እንሆን ዘንድ እኛን ከሞት በማስነሣቱ፣ አዲስ ወገን፣ "የአምላክ-ሰው ወገን" ሆንን።
   - ቸ. ሁለተኛ ቆሮንቶስ 3፡18፣ "እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን" ይላል፤ ሮሜ 12፡2 በአእምሮ መታደስ እየተለወጥን ስለመሆናችን ይናገራል።
   - ኀ. ፊልጵስዩስ 2፡15 በመጥፎና በጠማማ ትውልድ መካከል ያለ-ነውር እና ነቀፋ የሌለብን የእግዚአብሔር ልጆች እንደ ሆንን፣ በመካከላቸውም በዓለም እንደ ብርሃን እንደምናበራ ይናገራል።
   - ነ. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ነገር እንኳ ለራሱ ማስገዛት በሚችልበት አሠራሩ መሠረት፣ የተዋረደው ሰውነታችንን የእርሱን የክብሩን ሰውነት እንዲመስል ይለውጠዋል—3፡21።
   - ኘ. ክርስቶስ ሲገለጥ፣ ሙሉበሙሉ፣ ፈጽሞ፣ እና በትክክል ልክ እንደ እርሱ እንሆናለን፣ ምክንያቱም እርሱን እንዳለ እናየዋለንና—1 ዮሐ. 3፡1።
   - አ. ይህ ሁሉ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ይጠናቀቃል፤ ራእይ 4፡3 "ተቀምጦም የነበረው እርሱ [እግዚአብሔር]... የኢያስጲድን...ዕንቍ ይመስል ነበር" ይላል፤ የእግዚአብሔር፣ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ የነበረው መልክ ልክ እንደ ኢያስጲድ ነው።

ከ. በራእይ 21 መሠረት የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ብርሃን ልክ እንደ ከቡሩ ድንጋይ፣ እንደ ኢያስጲድ ድንጋይ ነው (ቁ. 11)፤ ቅጥሯ የተገነባው በኢያስጲድ ነው፣ የቅጥሯም መሠረት ኢያስጲድ ነው (ቁ. 18፣ 19)፦

1. በመጨረሻ፣ እግዚአብሔር እና ሰው፣ ሰው እና እግዚአብሔር፣ ሁሉም የኢያስጲድ መልክ ይኖራቸዋል፤ ስለዚህ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መደምደሚያ እና ማጠናቀቂያ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም—መለኮት ከሰብእና ጋር ተዋሕዶ—ናት፤ መለኮት የሰብእና ማደሪያ ስፍራ ይሆናል፣ እንዲሁም ሰብእና የመለኮት ቤት ይሆናል።
2. በዚህች ከተማ የእግዚአብሔር ክብር በብሩህነት እና በታላቅ ውበት በሰው ተገልጧል፤ አሁን አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ለመሆን እና የእግዚአብሔርን መልክ—ኢያስጲድ—ለመምሰል መለኮት በመደረግ ሂደት ውስጥ ነን—ቁ. 11፣ 23።
3. በዚህ ዘመን መጨረሻ እግዚአብሔር ሰውን አምላክ ለማድረግ ሰው ሆነ፣ ይኸውም በግጻዌ መለኮቱ ሳይሆን በሕይወት እና በባሕርይ ከእርሱ ጋር አንድ ዓይነት ለማድረግ የሚለውን እውነት እያስተማርን እና እየሰበክን ነው፣ ይህንን እውነት መስማት ታላቅ በረከት ነው።
4. በመጨረሻም፣ አምላክ-ሰዎች፣ አሸናፊዎች፣ ድል-ነሺዎች፣ በኢየሩሳሌም ያሉ ጽዮን ይሆናሉ፤ በእያንዳንዱ የዕለት ተዕለት ኑሮአችን የአምላክ-ሰው ኑሮ በመኖራችን በታሪክ ታይቶ የማይታወቅ አዲስ መነቃቃት ይመጣል፣ ይህም ይህንን ዘመን ይፈጽማል—መዝሙረ ዳዊት 48፥2'ን እና የግርጌ ማስታወሻ 1'ን ያንብቡ።

## II. የኤርሚያስ መጽሐፍ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የመሆንን መርህ ያሳየናል፦

ሀ. ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የመሆን መርህ—የሕይወት ዛፍ መርህ—እና የመልካምና የክፉ እውቀት ዛፍ መርህ ተጻራሪነት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሁለቱን መሠረታዊ ኃጢአቶችን በሚገልጠው በኤርሚያስ 2፥13 ታይቷል፦

1. የመጀመሪያው ኃጢአት እንደ የሕያው ውኃዎች መፍለቂያ፣ እንደ ምንጭ ያሕዌን መተው ነበር፤ ሁለተኛው ኃጢአት ውኃን መያዝ የማይችሉ የተቀደዱ ጉድጓዶችን ለራሳቸው መቆፈራቸው ነበር።
2. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው መርህ እግዚአብሔር የመረጠው ሕዝቡ ከእርሱ በቀር ሌላ ምንም ነገር እንደ ምንጫቸው እንዲወስዱ አለመፈለጉ ነው፤ እንደ ሕይወት እግዚአብሔርን በሚያመለክተው በሕይወት ዛፍ ፊት ለፊት ሰውን በማቆም፣ እግዚአብሔር እያመለከተ የነበረው ነገር ሰው ሌላ ምንም ነገርን ሳይሆን ከሕይወት ዛፍ እንዲካፈል እንደፈለገ ነው፤ ከሕይወት ዛፍ መካፈል እግዚአብሔርን እንደ ልዩና ብቸኛ ምንጫችን፣ እንደ የሁሉ ነገር ምንጫችን መካፈል ነው—ዘፍ. 2፥8-9።
3. ሁለተኛው ኃጢአት የእግዚአብሔር ሕዝብ በእግዚአብሔር ያለመታመናቸው ነገር ግን ለገዛ ድሰታቸው የሆነ ነገርን በራሳቸው ለመሥራት ማድረግ የሚችሉትን ማንኛውንም ነገር ለማድረግ በራሳቸው መታመናቸው ነበር፤ ኃጢአት እግዚአብሔርን መተው እና የሆነ ነገርን በራሳችን እና ለራሳችን ማድረግ ነው።
4. እነዚህ ሁለት መሠረታዊ ኃጢአቶች እግዚአብሔርን የሚያመለክተውን የሕይወትን ዛፍ እና ሰይጣንን የሚያመለክተውን የመልካም እና የክፉ እውቀት ዛፍን ያሳዩናል (ቁ. 8-9፣ 16-17)፤ እስራኤል ከሕይወት ዛፍ ወደ እውቀት ዛፍ፣ ከሕያው ውኃዎች ምንጭ ወደ ጉድጓዶች (ጣዖታት) ትኩረታቸውን ስተው ነበር።

ለ. እግዚአብሔር ከሰው ጋር አንድ ለመሆን ያለው መሻቱን ለማመልከት ሰውን በሕይወት ዛፍ ፊትለፊት አስቀመጠው፣ ይኸውም የሰው ሕይወት፣ የሕይወት አቅርቦት እና ሁሉ ነገር ለመሆን ነው—ቁ. 8-9፦

1. የሕይወት ዛፍ እንደ የእግዚአብሔር ብልጥግናዎች ሁሉ አካል-መልበስ ለምግባችን የተሰቀለውን (እንደ ቁራጭ እንጨት በዛፉ የተመለከተውን—1 ጴጥ. 2፥24) እና ከሞት የተነሣውን (በእግዚአብሔር ሕይወት የታየውን—ዮሐ. 11፥25) ክርስቶስ ያመለክታል።
2. የሕይወትን ዛፍ መብላት፣ እንደ የሕይወት አቅርቦታችን ክርስቶስን መደሰት፣ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ከሁሉ ይልቅ አስፈላጊ እና ዋና ጉዳይ መሆን አለበት፤ እርሱን በመብላት እርሱን መቀበል ማለት ከእኛ ጋር አንድ ለመሆን በሕይወታዊ እና በገንባ-አፍራሻዊ መንገድ ራሱን ከእኛ ጋር ማዋሐዱ ማለት ነው—ራእ. 2፥7፤ ዮሐ. 6፥57፣ 63፦
   - ሀ. ጌታ የተናገራቸው ቃሎች መንፈስና ሕይወት ናቸው፤ ይህ የሚያሳየው ጌታ የተናገራቸው ቃሎች የሕይወት መንፈስ አካል መልበስ መሆናቸውን ነው—ቁ. 63፦
     - (1) እርሱ አሁን በትንሣኤ ሕይወት-የሚሰጥ መንፈስ ነው (1 ቆሮ. 15፥45)፣ መንፈስ በእርሱ ቃላት ውስጥ አካል ለብሷል።
     - (2) መንፈሳችንን በማንቀሳቀስ በጸሎት እና በልመና ሁሉ የእርሱን ቃሎች ስንቀበል (ኤፌ. 6፥17-18)፣ ሕይወት የሆነውን መንፈስ እናገኛለን።

ለ. ክርስቶስን መብላት ማለት መንፈሳችንን በማንቀሳቀስ የሕይወት መንፈስ አካል መልበስ የሆኑትን ቃሎቹን መብላት፣ ቃሎቹን መቀበል ነው—ኤር. 15፥16፤ ኤፌ. 6፥17-18፤ 1 ጴጥ. 2፥2፤ ዕብ. 5፥13-14፤ ሕዝ. 3፥1-4።

**III. የእግዚአብሔርን ቃል ለመውሰድ፣ ለመቀበል እና ለመጠበቅ፣ ከእርሱ ጋር ፈጽሞ አንድ መሆን አለብን፦**

ሀ. የጎዶልያስ ጉዳይ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ያልሆነ ሰው ጉዳይ ነው፤ ጎዶልያስ የእግዚአብሔር ነቢይ የሆነውን፣ ኤርሚያስን በመንከባከብ ታማኝ ቢሆንም፣ የጌታን ቃል አልፈለገም ነበር፣ ምክንያቱም ይህ የእርሱ ልማድ አልነበረምና—ኤር. 40፥5-6፤ 13-14፦

1. ጎዶልያስ ከእርሱ ጋር አንድ ለመሆን እና ከእርሱ የሚመነጨውን ማንኛውንም ነገር ለመቀበል እግዚአብሔርን እንደምንጩ አልወሰደም፤ እርሱ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የነበረ ሰው ቢሆን ኖሮ፣ በመጀመሪያ ያደርገው የነበረው ነገር የእግዚአብሔርን ቃል መቀበል ነበር።
2. እንደ የሃሳቡ፣ የፈቃዱ፣ የልቡ መሻት እና የበጎ ደስታው መገለጥ የእግዚአብሔርን ቃል ለመውሰድ፣ ለመቀበል እና ለመጠበቅ፣ በእርሱ በመታመን፣ በእርሱ ላይ በመደገፍ እና ከእኔነት የሚመጣ ምንም አመለካከት የሌለን በመሆን ከእግዚአብሔር ጋር ፈጽሞ አንድ መሆን አለብን—ተዛ. 2 ቆሮ. 1፥8-9፣ እና ቁ. 12፣ የግርጌ ማስታወሻ 2።
3. የመጽሐፍ ቅዱስ፣ በተለይም የአዲስ ኪዳን መርህ፣ እግዚአብሔር ወደ እርሱ ውስጥ እንድንገባ፣ እርሱን እንድንቀበለው እና ከእርሱ ጋር አንድ እንድንሆን ራሱን ለእኛ መክፈቱ ነው፤ ያኔ እርሱ በእኛ ውስጥ ይሆናል፣ እኛም እርሱን እንደ ሁሉ ነገር በመውሰድ በእርሱ ውስጥ እንሆናለን—ዮሐ. 15፥4-5፤ 1 ዮሐ. 2፥28፤ 3፥24።
4. ሃሳቡን፣ ፈቃዱን፣ የልቡን መሻት እና በጎ ደስታውን ለመግለጥ በመጀመሪያ የምንወስደው ነገር ቃሉን ነው፤ ለአመለካከቶቻችን ወይም ለምርጫዎቻችን ግድ አንሰኝም፤ በዚህ መንገድ አቅርቦት እንዲሆንላቸው እርሱን ለመናገር ለእርሱ እንደ ሚናገርበት አፉ እንሆናለን—ኤር. 1፥6-9።

ለ. ጌታ ለኤርሚያስ፣ "የከበረውንም ከተዋረደው ብትለይ እንደ አፌ ትሆናለህ" ብሎ ነገረው—15፥19፤ 23፥29፣ ተዛ. ቁ. 16፦

1. ከክርስቶስ ውጭ ያሉትን ነገሮች እንደ ኪሳራ በመቁጠር፣ ክርስቶስን ለማግኘት፣ ለአማኞቹ ወድነት እንደ ሆነ የክርስቶስን ክቡርነትን፣ ከሁሉ የላቀ-ታላቅነትን፣ ከሁሉ የሚያልፍ ዋጋውን ለማየት የልባችን ዓይኖች ሊበሩልን ያስፈልገናል—ፊልጵ. 3፥7-8፤ 1 ጴጥ. 2፥7፣ ተዛ. ቁ. 4፣ 6።
2. ለሙሉ መዳናቸው ለእግዚአብሔር ሕዝብ እናድል ዘንድ፣ የሚመግብ ወተት እና ትኩስ ማር እንደምታፈስሰው የመልካሚቱ ምድር እውነታ ጌታን በቃሉ ውስጥ በመቅመስ፣ ድርሻችን ከሆነው ምግብ በላይ የጌታን ቃሎች እንደ ውድ መዝገብ መያዝ አለብን—ኢዮ. 23፥12፤ 1 ጴጥ. 2፥2-5፤ መዝ. 119፥103፤ ዘዳ. 8፥8፤ መኃ. 4፥11።
3. ፍለጋ የሌላቸውን የክርስቶስን ብልጥግናዎች እንደ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጸጋ ለቅዱሳን ሁሉ ለማደል የእግዚአብሔርን ንግግሮች (መለኮታዊ መገለጥን የሚያመጣውን የእግዚአብሔር ንግግር፣ የእግዚአብሔርን የውስጥ ስሜት መገለጥ) መናገር እንችል ዘንድ የጌታን ቃሎች ከምድራዊ ብልጥግናዎች ሁሉ በላይ እንደ ውድ መዝገብ መያዝ አለብን—መዝ. 119፥72፣ 9-16፤ ኤፌ. 3፥8፤ 2 ቆሮ. 6፥10፤ 1 ጴጥ. 4፥10-11።

**IV. የእስራኤል ውድቀት እና ሽንፈት ምሥጢሩ የእግዚአብሔርን መገኘት ማጣታቸው እና ከዚያ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ አለመሆናቸው ነበር (ተዛ. ኢያ. 7፥3-4፤ 9፥14)፤ ከእግዚአብሔር ጋር ያሉ ሰዎች—አምላክ-ሰዎች—እያደረገን ካለው፣ በመካከላችን ብቻ ሳይሆን በውስጣችንም ካለው ከአምላካችን ጋር ሁልጊዜ አንድ መሆን አለብን፦**

ሀ. እንደ አምላክ-ሰዎች ከእርሱ ጋር በመመላለስ፣ ከእርሱ ጋር በመኖር፣ እና መላው ማንነታችን ከእርሱ ጋር በማድረግ ከጌታ ጋር አንድ መሆንን በተግባር መለማመድ አለብን (ሮሜ 8፥4፤ 2 ቆሮ. 2፥10፤ ገላ. 5፥16፣ 25)፤ እንደ ክርስቲያን ለመመላለስ፣ እንደ እግዚአብሔር ልጅ ለመዋጋት እና የክርስቶስን አካል ለመገንባት መንገዱ ይህ ነው፤ ከእርሱ ጋር አንድ በመሆን የጌታ መገኘት ካለን ነገሮችን በተመለከተ ጥበብ፣ የውስጥ-እይታ፣ ቅድመ-እይታ እና የውስጥ እውቀት ይኖረናል፤ የጌታ መገኘት ለእኛ ሁሉ ነገር ነው።

ለ. የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት በመሥራታቸው የነበራቸው ግትርነት ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ካለመሆናቸው የተነሣ ነው (ኤር. 42፥1—43፥2)፤ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ሆነው ቢሆን ኖሮ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በተቀበሉ እና ልቡን፣ ባሕርይውን፣ አእምሮውን እና ዓለማውን ባወቁ ነበር፣ ከዚህም በተጨማሪ በምድር ላይ የእርሱ ምስክር ይሆኑ ዘንድ ቅጽበታዊ በሆነ መንገድ እርሱን በኖሩት እና በእርሱ በተቀናበሩ ነበር።

ሐ. ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ያልሆኑ ሰዎች ፈቃዱን እና በጎ ደስታውን አይቀበሉም ነገር ግን የሚገልጡት የራሳቸውን አመለካከት ነው፣ የራሳቸውን ምርጫዎች ይከታተላሉ፤ ይህንን ማድረግ እንደ የሕያው ውኃዎች ምንጭ፣ መፍለቂያ እግዚአብሔር መተው እና ውኃ ሊይዙ የማይችሉ የተቀደዱ ጉድጓዶችን መቆፈር ነው—2፥13።

V. ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ለመሆን፣ ክርስቶስ ቤዛነታችን እና ጽድቃችን ይሆን ዘንድ እንደ የዳዊት ቁጥቋጥ ያስፈልገናል፤ ይህም ኢኮኖሚውን ያከናውን ዘንድ ሕይወታችን፣ የውስጥ የሕይወት ሕጋችን፣ አቅማችን እና ሁሉ ነገራችን ለመሆን ራሱን ወደ ማንነታችን ውስጥ እንዲያድል ሦስታንዱን አምላክ ወደ ውስጣችን ያመጣል፤ ይህ አዲሱ ኪዳን ነው (31፡33)፤ በመጨረሻም እግዚአብሔርን እናውቃለን፣ እግዚአብሔርን እንኖራለን፣ በግጻዌ መለኮት ሳይሆን በሕይወትና በባሕርይ አምላክ እንሆናለን ይኸውም እንደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ብዙዎች የተካተቱበት መገለጡ እንሆን ዘንድ ነው—23፡5-6፤ 31፡31-34፤ ራእ. 21፡2።

*© 2020 Living Stream Ministry*